# አካባቢ ጥበቃ

የጉለሌ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት
Gullele Environmental Protection Office

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጉለሌ ክ/ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት መጽሄት

ቅፅ. 1 | ታህሳስ 2018





አካባቢ ጥበቃ ለዘላቂ ልማት!!

www.gulleleepo.gov.et

# የጉለሌ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት

የጉለሌ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት
Gullele Environmental Protection Office

## ራዕይ / Vision

የጉለሌ ክፍለ ከተማ በ2022 ከአካባቢ ብክለት ተጠብቃ ውጤታማ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም የሚካሄድባት ለነዋሪዎቿ ጤናማና ተስማሚ የሆነች ተመራጭ ከሆኑ ከአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች አንዷ ማድረግ ነው።

## ተልዕኮ /Mission/

የጉለሌ ክፍለ ከተማን ሕዝብ ግንዛቤና ተሳትፎን በማሳደግ በጥናትና በቴክኖሎጂ የታገዘ የብክለትና የአረንጓዴ አካባቢዎች ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ፣ ልማትን ከአካባቢ ጋር በማጣጣም፤ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን በማላመድ /Adaptation/ እና በማስተሰረይ /mitigation/፤ እንዲሁም ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር በማሳደግ የከተማዋ ነዋሪ በንፁህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብቱ እንዲጠበቅ ማድረግ፡

## ዕሴቶችና እምነቶች / Values and values

- አለማቀፋዊነት /Globalization/
- ሚዛናዊ የተፈጥሮ ሀብት /Balanced natural resources/
- የአካባቢ ተቆርቋሪነት / Environemental concern/
- የአካባቢ ተስማሚነት / Environmental Friendly/
- ብዝሃ ሕይወት መጠበቅ /Biodiversity conservation/
- አሳታፊነት/Participation/
- ዘለቄታዊነት /Sustainability

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን



## አቶ ዲዳ ድሪባ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
ዋና ስራ አስኪያጅ

S ABABA ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHO

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን



**አቶ አሰግደዉ ሀይለጊዮርጊስ**
የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትልና
የስነምህዳርና ማዕድን ልማት ዘርፍ ኃላፊ



**አቶ ሙሉቀን ዮናስ**
የአዲስ አበባ  አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትልና
የአካባቢ ብክለትና አየር ንብረት ለዉጥ ዘርፍ ኃላፊ

# የጉለሌ ክ/ከተማ
# አስተዳደር



## አቶ ወልዴ ወገሴ
የጉለሌ ክፍለ ከተማ
ዋና ስራ አስፈጻሚ



## አቶ ይከበር ስማቸዉ

የጉለሌ ክ/ከተማ ብልጽግና ፓርቲ
ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ



## አቶ ሰለሞን ታደሰ

የጉለሌ ክ/ከተማ ም/ዋና ስራ አስፈጻሚና
የስራና ክህሎት ጽ/ቤት ኃላፊ



# ማውጫ ገጽ

## የጉለሌ ክ/ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት መጽሔት


የኃላፊዉ መልዕክት 4

የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት 5

የባለድርሻ አካላት ሚና በአካባቢ ጥበቃ 6





ጽ/ቤቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች 7

ጽ/ቤቱ ቡድኑ የሚሰጡ የአገልግሎት አይነቶች 9

የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 የህግ ጥበቃ እና ክልከላ 12

የሸገር ወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት የክፍለ ከተማውንና ከተማውን ገፅታ ለመለወጥ እየተሰራ እንደሚገኝ ተገለፀ 14





በ2017/18 በክረምት ወቅት የተተከሉ ችግኞችን ውሃ የማጠጣት እና ሌኞች የእንክብካቤ ስራዎችን ተከናወኑ። 15

የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን በመቀነስ ለነዋሪዎቿ ምቹና ጤናማ ክ/ከተማን ለመፍጠር በትኩረት እየሰራ መሆኑን የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት አስታወቀ። 17

አካባቢያችንን ከብክለት ለመከላከል ሁሉም የማህብረሰብ ክፍል የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ እንደሚገባ ተገለጸ። 18

በወንዞች ዳርቻ ልማት አካባቢን ውብ ፣ ፅዱ እና አረንጓዴ የማድረግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል ተባለ። 22




# የጽ/ቤቱ ኃላፊ መልዕክት



## ሀና ምህረቱ

**የጉለሌ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ**

የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ከተሰጠው ተግባርና ሃላፊት መሀከል ክፍለ ከተማዋን ከብክለት የጸዳች፣ ስነ-ምህዳሯ የተጠበቀና ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነችና ከሌሎች ክፍለ ከተሞች ጋር ተወዳዳሪ እንደትሆን ማድረግ ሲሆን የ2017ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ግምገማ እንደመነሻ በመጠቀም የተሰጡትን አስተያየቶች በማካተት የ2018 በጀት ዓመት እቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ወስጥ ከሴክተሮች ጋር የስራ ትስስር ፈጥሮና የጋራ እቅድ በማቀድና በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል። በተለይም የአካባቢ ብክለትንና ህገ ወጥነትን ከመከላከል አኳያ ከደንብና ከሰላምና ጸጥታ ጽ/ቤት ጋር ብዙ ስራ ተሰርቷል።

የአየር ንብረት ንቅናቄውን በተመለከተ በፕላስቲክ፣ በአየር፣ በውሃ፣ በአፈር፣ የድምጽ ብክለት መከላከል እና በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ትግበራ ላይ የክ/ከተማችን ነዋሪ እና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ግንዛቤን መፍጠርና ተሳትፎን የማሳደግ ሥራዎች በማከናወን የብክለት መከላከል ስርዓት ህዝቡን ባሳተፈ መልኩ ተሰርቷል። በዚህም መሰረት ባለፉት ወራት "ብክለት ይብቃ ዉበት ይንቃ" በሚል መሪ ቃል በአካባቢ ብክለት መከላከል ላይ ለተለያዩ የህሕብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ተችለዋል፡

በ2018 በጀት አመት የሚከናወኑ ስትራቴጂ ግቦች፣ ዓላማዎች ዋና ዋና ተግባራትን በመፈፀም በክፍለ ከተማችን ለሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልትን በእቅዳቸው አካተው እንዲተገብሩ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ፤ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ስርዓትን በማጠናከር የህግ ተከባሪነትና ተፈፃሚነትን በማሳደግ በድምጽ፣ በውሃና በአየር ብክለትን ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በመስራት፤ አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶች በመገምገም የይሁንታ ፈቃድ አግኝተው ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግና ነባር ፕሮጀክቶችን የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ማድረግ እንዲሁም ተቋማት የአካባቢ ኦዲት እንዲያስደርጉ ክትትል ማድረግ ተችሏል።



# የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባራት :-

1. የአካባቢ ጥበቃ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ አካባቢ እንዳይበከል የመከላከያ ስልት ይቀይሳል፣ አግባብ ያላቸውን አካላት ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያስተባብራል፤

2. የአካባቢ ጥበቃ፣ የተፈጥሮ ሀብትና የዘለቄታ አጠቃቀም እንዲኖርና እንዳይባክን ተገቢ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ስለ አካባቢ ጥበቃ በተለያዩ መድረኮች፣ አደረጃጀቶች እና በመገናኛ ብዙሃን ትምህርት ይሰጣል፤

3. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ልማትን ተግባራዊ እንዲሆን ያስተባብራል፤

4. ከኢንዱስትሪ ከሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ ዝቃጭ፣ ተረፈ ምርት፣ ቆሻሻ በሕግ መሠረት መወገዱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

5. ታዳሽና አማራጭ የኢነርጂ ምንጮች እና ቴክኖሎጂዎችን ያፈላልጋል፣ ያሻሽላል፤ ያሰርጻል፤ ያስፋፋል፤

6. ከተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ የአየር፣ የድምጽ እና የፍሳሽ ብክለትን በህግ መሰረት ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

7. የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ሌሎች አካባቢ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ አካላት የብክለት መከላከል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

8. የከተማው የካባና ሌሎች ተቆፋሪ ማዕድናት ሥፍራዎች ያላቸውን የማዕድን ክምችት መጠን ይለያል፤ ለልማት ያዘጋጃል፤ ከአደጋ ነጻ መሆኑን ያረጋግጣል፤

9. የካባ ማምረት ሥራ ለሚያካሂዱ ፈቃድ ይሰጣል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤

10. የተለያዩ ማዕድናት ቁፋሮ የተካሄደባቸውን ቦታዎች መልሰው የሚለሙበት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

11. የተለያዩ ዕፅዋት የሚተከሉበትን ቦታና የሚሰጡትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ለመናፈሻ፣ ለደን፣ ለወንዝ ዳርቻና ለሌላ አረንጓዴ ቦታ ልማት በተከለሉ ቦታዎች ላይ የሚተከሉትን ዕፅዋት አይነት በሚመለከት ያማክራል፤ ያስተዋውቃል፤

12. ልተሞከሩና የማይታወቁ ከአካባቢ ጋር ተስማሚና ጠቃሚ የሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች በከተማው ማልማት ለሚፈልጉ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፤

13. በመንግስትም ሆነ በግል የይዞታ ክልል የለሙ ዛፎችን ለመቁረጥ ሲፈለግ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከባለስልጣኑ ዕውቅናና ፈቃድ ውጭ እንዳይቆረጡ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

14. በአስተዳደሩ ይዞታ ስር የሚገኙ ጥብቅ የደን ቦታዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ የጋራ መገልገያ አረንጓዴ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

15. በተፋሰስና በአረንጓዴ አካባቢዎች ልማትና አገልግሎት ዘርፎች መሠማራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ነዋሪዎች ወይም ሌሎች አካላት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

16. ዓላማውን ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።



# የባለድርሻ አካላት ሚና በአካባቢ ጥበቃ

- ህበረተሰቡ የራሱን ቤት የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ በመያዝ ብሎኩን ከብክለት ነጻ ማድረግ ይገባዋል ።
- የአግልገሎት ሰጪእና የማምረቻ ተቋማት የአመራረት ሰርዓታቸውን ሃይል፤ግበዓት ቆጣቢና ቆሻሻን ወደሚቀንስ አሰራር ማሸጋገር ይገባቸዋል፤
- የትምህርት ተቋማት የአካባበቢብክለት በዛሬው እና በነገው ትውልድ እጣ ፋንታ ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተጽእኖ በማስተማር የባህል ለውጥ እንዲመጣ ማገዝ ይገባቸዋል፤
- የመንግስት ተቋማት የአካባቢ ደህንነትን ለማረጋገጥ የወጡ ህጎች፤ አሰራሮች ስታንደርዶች ስራ ላይ እንዲውሉ ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይገባቸዋል።
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ብክለት ለመካላከል በሚደረገው ጥረት ውስጥ የግንዛቤ ማስጫበጫ ስራዎችን እና ተጨባጭ ውጤት ያላቸው ፕሮጅቶችን ሊተገብሩ ይገባል።
- ወጣቶችና ሴቶች ብክለትን ለመካለከል በሚደረገው ጥረት ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን አለባቸው፤
- የሃይማኖት ተቋማት ብክለትን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ እራሳቸውን ግንባር ቀደም ከመሆን ባለፈ ተከታዮቻቸውን ማስተማር ይገባቸዋል፤

## በጉለሌ ክ/ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት የሚሰጣቸው ዝርዝር አገልግሎቶች

- ስለአካባቢ ብክለት፣ህጎችና የአፈፃፀም መመሪያዎች ለህብረተሰቡ ስልጠናና ግንዛቤ መስጠት
- ብክለት በሚያደርሱ ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ
- የብክለት መጠን በመለካት እርምጃ መውሰድ ፣

- የፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነዶችን በመገምገምና መቆጣጠር የማስተካከያ ሀሳብ መስጠት
- ስለአየር ንብረት ለውጥ፣ ህጎችና የአፈፃፀም መመሪያዎች ለህብረተሰቡ ስልጠናና ግንዛቤ መስጠት ፣

- ለአየር ንብረት ለውጥን በዘርፍ መ/ቤቶች በዕቅድ መካተቱን ማረጋገጥ
- ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ተጋላጭ የህበረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና ክትትል

- የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን የዲዛይንና የፕሮሞሽን ስራ በመስራት ለተጠቃሚዎች ማስፋፋት፥
- በአፈር መሸርሸር ምክንያት የተጎዱ ቦታዎችን በመለየት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች እንዲደረጉ ለሚመለከተው አካል በሪፖርት ያውቃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

- በፕላን ለአረንጓዴነት የተመላከቱ ቦታዎች ከህገ ወጥ ወረራ ስለመጠበቃቸው እና ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን የቁጥጥር ስራዎችን ይሰራል፤
- ስለ አካባቢ ጉዳዮች የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ የግንዛቤ ስራዎችን ይሰራል፤

- የአንጓዴ ቦታዎች ከወራሪ አረሞች፣ ከእጽዋት በሽታዎች እና ተባዮች መጠበቃቸውን በዳሰሳ ጥናት በመለየት የቁጥጥርና የክትትል ስራችዎችን ይሰራል፤
- ለዛፍ ቆረጣ ከሚሰጥ ፈቃድ ላይ የሮያሊቲ ክፍያ ብር ገቢ በማሰባሰብ የመንግስትን ገቢ ማሳደግ



# GREEN LEGACY

## አረንጓዴ አሻራ

**ኑ ኢትዮጵያን በዛፎች ጥላ እናስጠልላት!!**

**በጉለሌ ክ/ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት**



አቶ ወንድወሰን ሽፈራዉ
የአካባቢ ብክለት ክትትልና ቁጥጥር ቡድን መሪ

# በቡድኑ የሚሰጡ የአገልግሎት አይነቶች

- የብክለት ይወገድልኝ አቤቱታዎችን ማስተናገድ፣
- መልስተኛ የአልሚዎች ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህብረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነዶችን መገምገምና የብቃት ማረጋገጫ ይሁንታ መስጠት ፣
- አነስተኛ ለሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ማካሄድና ምላሽ መስጠት ፣
- የአካባቢ ብክለት ግንዛቤ ማስጨበጫና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚያስተዋውቁ የስልጠና መድረኮች በአካባቢ ጥበቃ ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ




## በቡድኑ የሚሰጡ የአገልግሎት አይነቶች

- በፕላን ለአረንጓዴነት የተመላከቱ ቦታዎች ከህገ ወጥ ወረራ ስለመጠበቃቸው እና ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን የቁጥጥር ስራዎችን ይሰራል፤
- የአንጓዴ ቦታዎች ከወራሪ አረሞች፣ ከእጽዋት በሽታዎች እና ተባዮች መጠበቃቸውን በዳሰሳ ጥናት በመለየት የቁጥጥርና የክትትል ስራችዎችን ይሰራል፤
- በክፍለ ከተማችን በአረንጓዴ አሻራ መርኃ ግብር በየዓመቱ የሚተከሉ ችግኞችን የጽድቀት መጠን ዳሰሳ ጥናቶችን በመስራት ግኝቱንና ውጤቱን ለከተማ ውበት ጽ/ቤት እና ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያሳውቃል፤ በግኝቱ መሰረት የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውንም ይከታተላል፤
- በዘርፉ ለተመረቁ እና በአረንጓዴ ልማት ስራዎች ላይ የማማከር አገልግሎት መሰጠት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤
- በአፈር መሸርሸር እና መከላት ምክንያት የተጎዱ ቦታዎችን በመለየት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች እንዲደረጉ ለሚመለከተው አካል በሪፖርት ያውቃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
- በግል፣ በመንግስት፣ በማህበራትና በተቋማት ይዞታዎች ላይ የተተከሉ ዛፎች ለምርት ሲደርሱ፣ በሰው እና በንብረት ላይ ጉዳት ሲያደርሱ፣ ከመብራት ጋር ንክኪ ሲፈጥሩ እና መሰረተ ልማት የሚያበላሹ መሆናቸው በባለሙያ ከተረጋገጠ የቆረጣ እና የምልመላ ፈቃድ ይሰጣል፤
- ለዛፍ ቆረጣ ከሚሰጥ ፈቃድ ላይ የሮያሊቲ ክፍያ ብር ገቢ በማሰባሰብ የመንግስትን ገቢ በማሳደግ ረገድ እና ደኖች ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በመጨመር ስራዎችን ይሰራል።
- ስለ አካባቢ ጉዳዮች የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ የግንዛቤ ስራዎችን ይሰራል፤




# በቡድኑ የሚሰጡ የአገልግሎት አይነቶች

ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ፣ ዜጎች በምቹና ተስማሚ አካባቢ የመኖር መብታቸውን እውን ለማድረግ እንዲሁም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ተግባራዊ ለማድረግ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች በመንግሥት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል።ነገር ግን ከተማችን ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ይበልጥ ተጋላጭ ሆናለች። ለዚህም መገላጫው ወደ ከተማዋ አየር የሚለቀቁት የሙቀት አማቂ ጋዞች መጨመርና ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆን ለጎርፍ አደጋና የአየር ሙቀት መጨመር ምክንያት ሆኗል ። ማንኛወም የልማት ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት አሉታዎ ተፅዕኖ አስቀድሞ ሳይገመገሙ በስፋት ወደ ስራ በመግባታቸው በከተማዋ አካባቢ ላይ ተጨማሪ ጉዳት ከማስከተላቸውም በተጨማሪ አካባቢና ልማት ተጣጥመው እንዳይሄዱ ምክንያት ሆኗል። በከተማ ደረጃ የታዳሽ ሃይል አጠቃቀምና አማራጭ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ስርዓት መዘርጋት ፤ማስፋት፤ ማስረፅና ማጎልበት ባለመቻሉ በአየር ብክለት፤ በደን ኃብት እና በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ላይ ይገኛል፤በመዲናችን አዲስ አበባ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በመልም አስተዳደር ዘርፎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል።

ይህንን ለመቋቋም የኢፌዲሪ መንግስት የችግሩ አሳሳቢነትና አንገብጋቢነት በመረዳት ይህንን ተግባር ውጤታማ በሆነ መልኩ በመምራት ችግሩን ለመቀልበስ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተቋም መዋቅር በየደረጃው በአዋጅ ቁጥር 74/2014 መሰረት እንዲቋቋም ተደርጓል። የጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ በዚሁ መሰረት የተቋቋመ ነዉ፤በዚህ ጊዜ እየተሰሩ ካሉ መልካም ጅምር ስራዎች በተጨማሪ የሁላችንም ድርሻ እና ትግባራዊ እንቅስቃሴ የሚፈልጉ ናቸዉ።

## በቡድኑ የሚሰጡ የአገልግሎት አይነቶች

- የኢነርጂ ቴክኖሎጂና ምንጮች ላይ የግንዛቤ ስልጠና መስጠት፣
- የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎችን የተመለከቱ የግንዛቤ ትምህርት መስጠት፣
- የኢነርጂ ቴክኖሎጂና ምንጮች አጠቃቀምና አመራረት ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት ፣
- የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅና አጠቃቀሙን የማስረጽ ስራ መስራት

# የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 የህግ ጥበቃ እና ክልከላ

ኢትዮጵያ አሁን ላይ በሰፊው በገጽታ ግንባታ እና የከተማ ውበት ስራዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል እየተሰሩ ይገኛል፡፡ለዚህም ሁነኛ ማሳያ እና ተጠቃሽ የሚሆነው የመንገድ ኮሪደር ልማት ነው፡፡ ሳሎንን አስውቦ ጓዳውን መተው እንዳይሆን ይህን የልማት ስራ ዘርፈ ብዙ ማድረግ በማስፈለጉ ወንዞችን የማልማት እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛል፡፡ ከዚህም አላማ ሰፋ ባለ መልኩ ወንዞች ላይ በከፍተኛ በሆነ ደረጃ እየደረሰባቸው ያለውን ጉዳት እና ብክለት ለመቆጣጠር እና አስገዳጅነት ይኖረው ዘንድ በህግ ታቅፎ ይገኛል፡፡

በፌዴራል ደረጃ የትኛውንም የውሃ አካል አጠቃቀም እና ዳርቻዎችን እርቀት ለመወሰን በ2017 በረቂቅ ደረጃ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ እና ሂደት ላይ ያለ ነው፡፡ይህም ረቂቅ ከወንዝ በተጨማሪ ኩሬ ፣ሃይቅ፣ጠበብ ባሉ በውሃ የተሸፈኑ ስፍራዎችን እና ባህርን የሚያጠቃልል እና በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ላይ የተፈጻሚነት ወሰን ያለው ነው፡፡

በመዲናችን አዲስ አበበ ስንመጣ በአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ተወልዶ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 በሚል የልጅነት ስም ተሰቶት ለነዋሪው የተበረከተ ሲሆን በቀጣይም ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል እና የከተማው የአስተዳደር አካላት በመቀናጀት ተፈጻሚነቱን የሚያረጋግጡ ይሆናል፡፡

## ወንዝን ጨምሮ አካባቢን የመጠበቅ አስፈላጊነት ጽንሰ ሀሳብ/መላምት /theory/

ይህ መላምት ወይም ሀሳብ የሚለይልን ተፈጥሮን ወንዝንም ጨምሮ የሚደረግላቸውን ጥበቃ አስፈላጊነት ለምን እንደሆነ ለመለየት የሚረዳ ነው፡፡ ሁለት አይነት ሃሳቦች በአካባቢ ጥበቃ አቀንቃኞች እና ተሟጋቾች ይሰነዘራሉ:

**1ኛ ፡- ተፈጥሮን የምንጠብቀው ለሰው ልጅ ካላቸው ጥቅም የተነሳ ነው የሚሉ ሲሆን (Antropocenteric) በሚል ቲዮሪ የሚታወቁ ናቸው ፡፡**

ለምሳሌ፡- የወንዝን ብክለት የምንከላከለው ወንዞች ለሰው ልጅ ለመጠጥ ፣ሲጠበቁ ካላቸው ውበት እና ንጽህና የሰውን አእምሮ የሚያድሱ በመሆናቸው ነው፡፡

**2ኛ ፡- ተፈጥሮን የምንጠብቀው ለሰው ልጅ ካላቸው ፋይዳ ሳይሆን እራሳቸውን ችለው መብት ስላላቸው እና መጠበቅ ስላለበቸው ብቻ ነው፡፡** ይህም ማለት ለሰው ልጅ ጥቅም ቢሰጡም ባይሰጡም መጠበቅ አለባቸው በማለት የሚሟገቱ ናቸው፡፡ የሀገራችን የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ወንዝን ጨምሮ ከማን አንጻር ማለትም ከአካባቢ አንጻር ወይስ ከሚሰጡት ጥቅም አንጻር መሆኑን የሚዳሰስ ይሆናል፡፡



**የደንብ ቁጥር 180/2017 አስፈላጊነት**

**የደንብ ቁጥር 180/2017 አስፈላጊነት በሁለት አይነት መንገድ ተከፍሎ የሚታይ ነው፡-**

**ወቅታዊ ወይም አፋጣኝ ምክንያት ፡- ወንዞች አሁን ላይ በሰው ሰራሽም ይሁን በሌላም ምክንያት መጠናቸው እና ጥራታቸው ላይ ጉዳት እየደረሰ እንዲሁም ውሃን የመያዝ እና እንዳይደርቁ የሚከላከሉ የእጽዋት አይነቶች መመናመናቸው በተጨማሪም በከፍተኛ ብክለት የአካባቢን ገጽታ እያጠፉ በመሆናቸው ነው፡፡**

**መሰረታዊ (መነሻ) ምክንያት- ሁሉም ሰዎች በንጹህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት ከሰብዓዊ መብቶች በሶስተኛነት ደረጃ የሚመደብ ( 3rd generation right ) በመሆኑ እና ይህም በሕገ-መንግስታችን አንቀጽ 40 ንኡስ 1 እዉቅና/ጥበቃ( recognition ) ያገኘ መብት ነው፡፡ ታዲያ መንግስትም ይህን መሰረታዊ የዜጎች መብትን የማስከበር ግዴታ ያለበት በመሆኑ እና አስገዳጅነት እንዲኖረው በማይፈጽሙ አካላት ላይ ተመጣጣኝ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊያሶስድ የሚችል ዝርዝር የህግ ማእቀፍ በማስፈለጉ ይህን ደንብ ወቷል፡፡**

**ክልከላ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 በውስጡ ብክለትን ለመቆጣጠር ያስችላል ተብሎ የሚታሰቡ ክልከላዎች እና ቅጣቶችን አስቀምጧል፡፡ በዋናነት መኖሪያ ቤቶች ፣ከአምራች ድርጅቶች እና ከተቋማት የሚጣሉ የትኛውም አይነት ደረቅ ቆሻሻ ፣ኬሚካል፣ የሚለቀቁ የሽንት ቤት ፍሳሽ እና የትኛውም አይነት ያልተጣራ ፍሳሽ ወደ ወንዝ ወይም ከወንዝ ጋር በተያያዙ መስመሮች መልቀቅ እንዲሁም በወንዝ 30 ሜትር ወሰን ውስጥ የትኛውንም ከመዝናኛ እና የአካባቢ ልማት ውጪ ያሉ ግንባታ ማካሄድ የተከለከለ ነው፡፡ይህንንም ከደንቡ አንቀጽ 7 መሰረት የተደነገገ ነው፡፡**






# ቅጣት

## አስተዳደራዊ እርምጃ

የጉዳቱን መጠን እና የመክፈል አቅምን ታሳቢ በማድረግ ለግለሰብ እና ለተቋም በመለየት የተለያየ ቅጣቶች እንደተቀመጡ የደንቡ አንቀጽ 17 ያሳያል፡የተቋሙን ፍቃድ መሰረዝ ፣ማሸግ፣ ድርጊቱን የማስቆም ጉዳት ደርሶም ከሆነ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ማድረግ ተካተዋል።

## የገንዘብ ቅጣት

እንደየጥፋቱ አይነት ከ 1000 እስከ 400000 ብር ድረስ የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት

## ከውል ውጭ የመነጨ ቅጣት

በወንዞች ብክለት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በብክለቱ ምክንያት ጉዳት እንደ ደረሰበት በማስረዳት ለደረሰበት ጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት አለው።



## የወንጀል ቅጣት

በ1997 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 517 መሰረት ወንዝን ሆን ብሎ የበከለ ወይም የመረዘ እስከ 15 አመት ድረስ ጽኑ እስራት የሚተላለፍበት ሲሆን በቸልተኝነት ከሆነ እስከ 6 ወር የሚደርስ የእስር ቅጣት እንደሚተላለፍበት ይደነግጋል።

## አስፈጻሚ ባለድርሻ አካላት

የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 ተፈጻሚነቱን ለማረጋገጥ ከግለሰብ እስከ አስተዳደር አካላት የሚሰሩ ሲሆን አስፈጻሚ አካላት በቅንጅት የሚሰሩ ይሆናል።ለአብነት ያህል የአ.አ ከተማ አስተዳደር የከተማ ዉበትና አረንገዴ ልማት ቢሮ ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፣ የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መንገድ ባለስልጣን ሲኖሩ ወደፊትም በትስስር እና ቅንጅት ስምምነት ባለድርሻ ሆነው የሚገቡትን ይጨምራል።







## የሸገር ወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት የክፍለ ከተማውንና ከተማውን ገፅታ ለመለወጥ እየተሰራ እንደሚገኝ ተገለፀ ፡፡

የሸገር  የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ ሥራ አፈጻጸም ሂደትን ያለበትን ሁኔታ የኪነጥበብ ባለሞያዎችና ከከተማ የመጡ የክብር እንግዶች እንዲሁም ተጽኖ ፈጣሪ ሰዎች ጉብኝት አደረጉ፡፡

በጉብኝቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊና የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ ጥላሁን ወርቁ   እንደተገለፀው የሚሰራውን ፕሮጀክት በማወቅና ለሌሎች አካላት ግንዛቤ በመፍጠር የሚችልበት አግባብ በማስቀጠልና ህብረተሰቡን ተጠቃሚነቱን በማጉላት ፕሮጀክቱ  በታቀደለት ጊዜ በጥራትና  በውጤት ለማጠናቀቅ የኪነጥበብ ባለሞያዎች ያላቸው ሚና ከፈተኛ እንደሆነ ተጠቅሷል ፡፡ የሸገር የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት የአካባቢውን ተፈጥሮአዊ ስነ ምህዳር በመጠበቅ  መልኩ ሰው ተኮር የሆነ ፕሮጀክት እንደሆነናበተለይም የኮንሶ ተፈጥሮን መንከባከቢያ የእርከን ስራ የጤና እጽዋቶችን ያካተተ እንደሆነናሰፊ የሆነ ፕሮጀክት መሆኑን ተጠቁሟል ፡፡

የጉለሌ  ክፍለ ከተማ ምክትል  ዋና ስራ አስፈጻሚና ስራና ክህሎት ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሰለሞን ታደሰ በበኩላቸው የሸገር የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት የአካባቢውን ተፈጥሮአዊ ስነ ምህዳር በመጠበቅ ሰው ተኮር የሆነ ፕሮጀክት ነው በተለይም የኮንሶ ተፈጥሮን መንከባከቢያ የእርከን ስራ የጤና እጽዋቶችን በመያዝ ሰፊ የሆነ ፕሮጀክት መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

በመጨረሻም የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ለከተማዋ አዲስ ገፅታን የሚያላብስ፣ የቱሪስት መዳረሻነቷን የሚጨምር   እና ለነዋሪዎቿ   ውብና ማራኪ ገፅታን የሚያጎናፅፍ ፕሮጀክት በመሆኑን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን አቶ ሰሎሞን ታደሰ ገልጸዋል፡፡



# የጉለሌ ክ/ከተማ አስተዳደር ባለሙያዎችና አመራሮች በ2017/18 በክረምት ወቅት የተተከሉ ችግኞችን ውሃ የማጠጣት እና ሌቾች የእንክብካቤ ስራዎችን አከናወኑ።

በፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የጉለሌ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ወልዴ ወገሴ በንግግራቸው እንደሀገር የተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ ልማት የተስተካከለ የዝናብ ስርጭት እንዲኖር፣ ለኑሮ ተስማሚ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር፣ የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግና፣ የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት ፋይዳው የጎላ በመሆኑ ችግኝ ተክሎ ማሳደግ የዘውትር ተግባራችን መሆን አለበት ሲሉ ተናግረዋል።



የጉለሌ ክፍለ ከተማ ብልፅግና ፓርቲ ቅ/ፅ/ቤት ሃላፊ አቶ ይከበር ስማቸው በበኩላቸው በችግኝ እንክብካቤ መርሃ ግብሩ ላይ እንደተናገሩት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የመተባበርና የአንድነት ውጤት ማሳያ መሆኑን ገልጸው የሚተከሉ ችግኞች የአየር ንብረት ለውጡን ከመከላከል ባሻገር ለከተማው ውበት የሚሰጡና ለምግብነት የሚውሉ በመሆናቸው መትከል ብቻውን ውጤት ባለመሆኑ የተተከሉ ችግኞችን መንከባከብ የሁላችንም ሃላፊነት ሊሆን ይገባል ብለዋል።





# የጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ከUNDP ኦርጋናይዜሽንጋር በመተባበር በንብ ማነብ ሙያ ዘርፍ ያሰለጠናቸውን አባወራዎችና እማወራዎች አሰልጥኖ አስመረቀ።

የጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ከUNDP ኦርጋናይዜሽን ጋር በመተባበር ለአየር ንብረት ተጋላጭ ለሆኑ አካባቢዎች በክፍለ ከተማው ወረዳ 6 የእንጦጦ ደን አካባቢ ላይ የሚኖሩ በኑሮአቸው ሊደጎሙ ለሚገቡ የህብረተሰብ ክፍሎች 70 አማወራዎችና አባወራዎች በንብ ማነብ አሰልጥኖ አስመረቀ።

በምርቃት ስነ ስርዓቱ ላይ የጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ሃና ምህረቱ እንደተናገሩት እንደ ክፍለ ከተማ ሰው ተኮር የሆኑ ስራዎችን በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ሲሆን የዛሬው ምርቃት የደን አካባቢ ነዋሪዎች ገቢ መፍጠሪያ እንዲሆን በማድረግ የአካባቢውን ተፈጥሮ ሃብት ተንከባካቢ እንደሆኑ ገልጸው በንብ ማነብ ዘርፍ አሰልጥኖ ስራ ዕድል ዕድል እንዲያገኙ ተሰርቷል ህብረተሰቡ የሚኖርበትን አካባቢ የሚገኘውን የደን ስፍራ ከጎጂ ነገሮች በመጠበቅ የኑሮ ሁኔታዎችን በማሻሻል ጠንክሮ መስራት ይገባል ብለዋል።

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስልጠና ክፍል ምክትል ኃላፊ አቶ ደመላሽ ተስፋዬ በበኩላቸው ሰልጣኞች በንድፈ ሃሳብና በተግባር የተደገፈ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ያገኙትን ስልጠና ወደ ተግባር መቀየርና ምርትና ምርታማነታቸውን ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል።





## የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን በመቀነስ ለነዋሪዎቿ ምቹና ጤናማ ክ/ከተማን ለመፍጠር በትኩረት እየሰራ መሆኑን የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት አስታወቀ።



የጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በአየር ንብረት ለውጥ አያያዝ፣ በአካባቢ ብክለት መከላከልና በብዝሃ ሕይወት ዙሪያ  በተመለከተ  ለተለያዩ ለሲቪክ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥቷል።

በስልጠናው መድረክ የተገኙት የጉለሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ማሩ መንግስቱ እንደገለጹት  ክፍለ ከተማችን ሰፊ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ያላት በመሆኗ ይህንን ሀብት ለመጠበቅና በአግባቡ ለመጠቀም ሰፊ የሆነ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ ስራዎች በመስራት እንዲሁም ከተማችን ከተጋረጠባት ከፍተኛ የብክለት ችግር ለመታደግ የበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት ብክለት የሚያደርሱ ተቋማት በመለየት ልማት እና አካባቢን ለማጣጣም አካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንዲሰሩ የማድረግ እንዲሁም ሕብረተሰቡ ስለ አካባቢ ያለዉን ግንዛቤ በተለያየ መንገድ በማሳደግ እና ድጋፍ በማድረግ ለአካባቢ ተቆርቋሪ ሕብረተሰብ ለመፍጠር ጥረት ይደረጋል ብለዋል ።

በቀጣይም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የአከባቢ ብክለትን በመከላከል  ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስርዓት ለመገንባት መረባረብ ይገባ ተመላክቷል።











# አካባቢያችንን ከብክለት ለመከላከል ሁሉም የማህብረሰብ ክፍል የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ እንደሚገባ ተገለጸ።

የጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በአካባቢ ብክለት፣ በብዝሃ ህይወትና ስነምህዳር እና በአየር ንብረት ለውጥ ዙርያ ለትምህርት ተቋማት የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ አባላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥቷል።

በስልጠናው ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ሀላፊ ወ/ሮ ሀና ምህረቱ እንደተናገሩት በብዝሃ ህይወት ጥበቃ፣ለአከባቢ ብክለትን ተቆርቋሪነት ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ በአከባቢ ላይ የሚደርሱ የአየር ብክለቶችን በመከላከል ንጹህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብትን ማረጋገጥ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የስልጠናው ተሳታፊዎችም የተፈጠረላቸው ግንዛቤ መሰረት በማድረግ አከባቢያቸውን ከብክለት ለመጠበቅና ለመከላከል የበኩላቸውን ሚና እንደሚወጡ ተናግረዋል።









# ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስርዓትን ለመገንባት የአካባቢ ብክለትን መከላከል እንደሚገባ ተገለጸ።



የጉለሌ ክፍለ ከተማ አከባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት የ2017 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀሙን እና የ2018 በጀት አመት እቅዱን ከሲቪክ ማህበራት ከባለድርሻ  አካላት ጋር ተወያይቷል።

ጽ/ቤቱ በተጠናቀቀው በጀት የአየር ፣ የውሃ ፣ የአፈርና የድምጽ ብክለቶች ዙሪያ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመስጠት በወንዝ ዳርቻ ልማቶች ላይ ብክለት መከላከያ መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ ወንዞችን መከላከል መቻሉ የአካባቢ ጥበቃና የልማት ስራዎች ማከናወኑን በሪፖርቱ ላይ ተብራርቷል ።

የክፍለ ከተማው አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ሃና ምህረቱ እንደተናገሩት በተጠናቀቀው በጀት አመት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የአካባቢ ግንዛቤ የማጎልበትና ከመቆጣጠር አንፃር ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በርካታ ስራዎች የተሰሩ መሆኑን በመግለጽ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት የመገንባት ስራውም ትኩረት  ተሰጥቶ መሰራቱን ተናግረዋል።



እየተተገበረ ላለው የአረንጓዴ ልማት መርሃ-ግብርም የችግኝ በማፍላትና የመትከያ ጉድጓድ በማዘጋጀት፣በመትከልና የጽድቀት መጠን ለማሳደግ በመንከባከብና በመጠበቅ ውጤታማ ስራ ማከናወን መቻሉን  ተገልጻል።

በቀጣይም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የአከባቢ ብክለትን በመከላከል የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን እና የአረንጓዴ ልማት ፕሮግራሞችን አጠናክሮ በመስራት  ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስርዓት ለመገንባት  በጋራ መረባረብ እንደሚገባ ተመላክቷል።

በተያያዘም የመልካም አስተዳደር ስራዎችና ቅንጅተዊ አሰራሮች ዙሪያ ውይይት አካሄዷል። ጽ/ቤቱ በ2017 በጀት ዓመት የላቀ አፈጻጸም ላበረከቱ ባለ ድርሻ አካላት ፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል።








በመትከል ማንሰራራት!!

## አረንጓዴ አሻራ የኢትዮጵያ ህዝብ ለችግሮች በቀላሉ እጅ የማይሰጥና ጠንካራ መሆኑን ማሳያ ነው !!

ኢትዮጵያ የበለፀገ ታሪክ፣ ባህልና ብዝሃነት ያላቸው ህዝቦች በጋራ የሚኖሩባት ሀገር ናት። እንደ ሀገር ድህነት፣ ድርቅ፣ ግጭትና የአየር ንብረት ለውጥ የመሳሰሉ ብዙ ፈተናዎች ገጥመዋታል። የሀገራችን ግብርና የኢኮኖሚው ዋና ምሶሶ ቢሆንም በዝናብ የዝናብ፣ የውሃ ሃብት እና የተፈጥሮ ስነ-ምህዳር ላይ ከፍተኛ ጥገኛ በመሆኑ ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ እጅግ ተጋላጭ ነው። የአየር ንብረት ለውጥ የኢትዮጵያን የልማት ግቦች ፈተና ላይ የሚጥል እና የሚሊዮን ህዝብ መተዳደሪያ የሆነውን ግብርና አደጋ ላይ የሚጥል ነው።

ኢትዮጵያ ግን በቀላሉ ተስፋ የምትቆርጥ ሀገር አይደለችም። እድገቷንና ብልፅግናዋን ለመጪዎቹ ትውልዶች ማስቀጠል የሚችል ለአየር ንብረት ለውጥ ተመራጭ የሆነ አረንጓዴ ኢኮኖሚን የመገንባት ራዕይ ያላት ሀገር ናት።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ እና ለማላመድ፣ የተራቆተ አካባቢውን ወደነበረበት ለመመለስ እና የተፈጥሮ ካፒታልን ለማሳደግ ደፋርና ትልቅ እርምጃ የወሰደች ሀገር ናት።

አረንጓዴ አሻራ የተባለ ግዙፍ ራዕይን የሰነቀ ፕሮጀክት በመተግበር በአራት ዓመት ውስጥ 25 ቢሊዮን ዛፎችን በመትከል፣ ሥራ በመፍጠር፣ የምግብ ዋስትናን በማሻሻል፣ የባዮዳይቨርሲቲ ሀብትን በማጎልበትና በረሃማነትን ለመዋጋት የሚያስችል ድንቅ ስራ በመስራት በርካታ ውጤቶች አስመዝግባለች።



ነገን ዛሬ እንትከል !!



# በጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በ6 ኪሎ ፣ በሽሮ ሜዳ እና እንጦጦ የለማው የኮሪደር ልማት ከተማዋን የሚመጥን ዘመናዊ ፕሮጀክት መሆኑ ተገለፀ።

በክፍለ  ከተማው የለማው የኮሪደር ልማት ስራዎችን በጉብኝቱ ላይ በብልፅግና ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የህዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ስዩም ከበደ ፣ የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ወልዴ ወገሴ፣ የጉለሌ ክ/ ከተማ ብልፅግና ፓርቲ ቅ/ፅ/ቤት ኃላፊ አቶ ይከበር ስማቸው : የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሰለሞን ታደሰ ፣ በብልፅግና ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ምክትል ኃላፊ አቶ ወንዱ አሰፋ ፣  በየደረጃው የሚገኙ የዘርፉ አመራሮች ፣  የሀይማኖት አባቶች ፣ አባገዳዎች ፣ ሀደስንቄዎች ፣ በጎ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ አርቲስቶች፣ ስፖርተኞች እና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች ጎብኝተዋል።



ለጎብኝዎች ገለጻ ያደረጉት የጉለሌ ክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ይከበር ስማቸው እንደተናገሩት ባለፉት ዓመታት መንግስት በርካታ ሰው ተኮር የሆኑ ተግባራትን ፣ የማይደፈሩ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን ፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ፣ የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶችን በማከናወን ከቁልቁለት ጉዞ አውጥቶ የማንሰራራት ጊዜያት ላይ ደርሰናል መጪዎች ጊዜያት የከፍታ ዘመን እንዲሆን ሁላችንም በተሰማራንበት ዘርፍ የላቀ ለውጥ የምንተጋበት መሆን ይገባል  ብለዋል።



የኮሪደር ልማቱ የአስፓልት መንገድ ዝርጋታ ፣የእግረኛ መንገድ ፣ የሳይክል መስመር ፣ የህጻናት መጫወቻ ቦታዎች ፣ የስፖርት ማዝወተሪያ ስፍራዎች ፣ የህዝብ መዝናኛ ፕላዛዎችና አረንጓዴ ፓርኮች ፣ መጸዳጃ ቤቶች ፣ የንግድ ሱቆች ፣ የመኪና ማቆሚያና ተርሚናሎች በውስጡ አካቷል።




# በወንዞች ዳርቻ ልማት አካባቢን ውብ ፣ ፅዱ እና አረንጓዴ የማድረግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል ተባለ።



በአዲስ አበባ ወደ 76 የሚጠጉ ገባር እና ዋና ወንዞች እንዳሉ የከተማዋ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መረጃ ያሳያል። ከከተማ እና ከአገልግሎት ተቋማት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ታዲያ በተለይ ወንዞችን ተከትሎ የሚደረግ ሰፈራ ወንዞቹ እንዲበከሉ ሲያደርግ እንደነበር የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አሰግድ ኃይለጊዮርጊስ ይናገራሉ።

የከተማ አስተዳደሩ ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለትን ለመከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 አውጥቶ ሥራ ላይ ማዋሉ ይታወቃል። ለረጅም ዓመታት የቆሻሻ መጣያ እና የኢንደስትሪ ፍሳሽ ማስወገጃ ሆነው የኖሩ የአዲስ አበባ ወንዞችም እየፀዱ ይገኛሉ።



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በመሆን በዚሁ ደንብ ዙሪያ ለከተማዋ ነዋሪዎች፣ ለአምራች እና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ሲሰጥ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ከሁለት ሺህ በላይ የሚሆኑ ግለሰቦች እንዲሁም የኢንደስትሪ እና የፋብሪካ ባለቤቶች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በካይ ነገሮችን ወደ ወንዝ ሲለቅቁ ተገኝተዋል።

በዚህም ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ አካላት 120 ሚሊዮን የሚጠጋ የብር ቅጣት መሰብሰቡን አቶ አሰግድ ኃይለጊዮርጊስ በኤፍ ኤም አዲስ የቀጥታ ስልክ መስመር ተገኝተው ተናግረዋል። ኅብረተሰቡ የሚሰጠውን የግንዛቤ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነቱን እንዲወጣ እና ለራሱም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ ንፁህ አካባቢን የመፍጠር ሚናውን እንዲወጣ አደራ ብለዋል።

# የአዲስ አበባ ከተማ የኮሪደር ልማት















# በጉለሌ ክ/ከተማ
## የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት


አድራሻችን

በጉለሌ ክ/ ከተማ አስተዳደር ህንጻ 8ኛ ፎቅ
እንገኛለን መጥታችሁ ተገልገሉ

አዘጋጅና አሳታሚ

0912689710